# PUBLICHOUSING

# የመንግሥት መኖሪያ ቤት

AMHARIC

የቪክቶሪያ መንግሥት በቁጥር መጠነኛ የሆነ የመንግሥት መኖርያ ቤቶችን አነስተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች ይሰጣል። የቤቶች ጽ/ቤት የመንግሥት መኖርያ ቤቶችን በማስተዳደርና በማደል ረገድ ይቆጣጠራል። በቅርቡ ወደ ቪክቶሪያ ለመጡ ሰዎች በተቻለ ፍጥነት የመንግሥት ቤት እንዲያገኙ በዚህ መመሪያ ውስጥ መረጃዎች እንዲያገኙ ይረዳል።

የመንግሥት ቤት ለማመልከት እንዲችሉ ለመርዳት የሚችሉ የኅብረተሰብ ድርጅቶች በዚህ መመሪያ ውስጥ ይገኛሉ [ማን ሊረዳኝ ይችላል? የሚለውን መመልከት]። እነዚህ ድርጅቶች እንዲያናድሩ እናሳስባለን። ስለ የመንግሥት ቤት ለማመልከት እውቀት ሲኖራቸው እናንተን ለመርዳት ዝግጁ ናቸው። የእነርሱ ግልጋሎት ነፃ ሲሆን መረጃዎች በሚስጢር የሚጠበቅና ከቤቶች ጽ/ቤት ጋር ግንኙነት አይኖረውም።

## ለመንግሥት መኖርያ ቤት ማን ማመልከት ይችላል?

የመንግሥት መኖርያ ቤት ለማመልከት ከፈለጉ ለቤቶች ጽ/ቤት የሚከተለውን ሁኔታ ማረጋገጥ የሚችል ሰነዶች ማቅረብ ያስፈልጋል፡

- የአውስትራሊያ ዜጋ ለመሆንዎ፣ ቋሚ ነዋሪ ወይም ጊዜያዊ የመከላከያ ቪዛ ካለዎት።
- በአሁኑ ወቅት ቪክቶሪያ ለመኖርዎ የሚያሳይ
- የራስዎ የሆነ ቤት፣ ዩኒት ወይም ፍላት የሌለዎ ለመሆኑ
- ከተፈቀደው መጠን በላይ ያልሆነ የራስዎ የገቢ ምንጭ የሚያሳይ [በአጠቃላይ አነስተኛ የገቢ ምንጭ ካለዎትና የሴንተር ሊንክ አበል የሚያገኙ ከሆነ ይፈቀዳል]።
- አውስትራሊያ ለመግባት በቤተሰብዎ በኩል ስፖንሰር ተደርገው ከሆነ የድጋፍ ቅንብሩ ውል ጊዜው ያበቃ ወይም ባለመግባባት ምክንያት ቅንብሩ ከፈረሰ
- የቤቶች ጽ/ቤት ያበደረዎን ማንኛውም ገንዘብ ከፍለው ወይም እየከፈሉ ለመሆንዎ [ለምሳሌ የማስያዣ ገንዘብ ብድር ከፍለው ወይም እየከፈሉ ለመሆንዎ]

## የመንግሥት መኖሪያ ቤት እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

የመንግሥት መኖሪያ ቤት ለማመልከት ከቤቶች ጽ/ቤት የማመልከቻ ቅጽ ማግኘት ይኖርብዎታል። የቤቶች ጽ/ቤቶች በሞላው ቪክቶሪያ ይገኛል። በአቅራቢያዎ ያለውን የቤቶች ጽ/ቤት ለማግኘት የስልክ ማውጫ በዋይት ፔጅስ ውስጥ ከA-K የሰብዓዊ አገልግሎት/ የመኖሪያ ቤት አገልግሎት ክፍል የሚለውን መመልከትነው።

አራት የመንግሥት መኖሪያ ቤት ማመልከቻ ቅጾች ሲኖሩ ለእያንዳንዱ የመደብ ዓይነት መግለጫ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። የርስዎን ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ ከአንድ መደብ በላይ ማመልከት ይችላሉ። የማመልከቻ ቅጹ በደንብ ካልተረዳዎት የቤቶች ጽ/ቤትና ብዙ የኮሚኒቲ/ሕብረተሰብ ድርጅቶች ሊረድዎት ይችላሉ[ማን ሊረዳኝ ይችላል?] የሚለውን መመልከት]።

## የቤቶች ጽ/ቤት እንዴት አድርጎ የእኔን ፍላጎት ሊያስስ ይችላል?

የቤቶች ጽ/ቤት የርስዎን ፍላጎትና ሁኔታ በማመዛዘን ያቀረቡትን ማመልከቻ በተዘረዘረት ሁለት የመጠባበቂያ ምዝገባዎች ማለት ተራ-መጠበቅ ወይም ቅድሚያ ቤት ማግኘት በሚለው ላይ በአንደኛው ይመደባሉ።

TENANTS UNION
of Victoria Ltd

## ተራ-መጠበቅ (Wait-Turn)

በአጠቃላይ ለመንግሥት መኖሪያ ቤት ለመመዝገብ ተራ-መጠበቅ በሚለው ይሆናል። በዚህ ዓይነት መመዝገብ ብዙ ጊዜ ያስጠብቃል።

## የቅድሚያ ቤት ማግኘት (Early Housing)

የመንግሥት መኖሪያ ቤት ቶሎ ብሎ ለማግኘት በቅድሚያ ቤት ምዝገባ በሚለው ቢሆንም በአስቸኳይ ቤት ለማስፈለጉ ማስረጃ ማሳየት መቻል ይገባል። የሚያስጠብቀው ጊዜ የሚወስነው እንደ ሁኔታው ማለት የሚያስፈልግዎ መኝታ ክፍሎች ቁጥርና ለመኖር የፈለጉበት አካባቢ ይሆናል።

በቅድሚያ ቤት ለማግኘት ሶስት ሁኔታዎች አሉ፤ እነሱም በተደጋጋሚ ቤት የለሽ መሆን፣ እርዳታ የሚሰጥበት መጠለያና ለየት ያለ የመኖሪያ ቤት ለሚፈልጉ ናቸው።

## በተደጋጋሚ ቤት የለሽ መሆን (Recurring Homelessness)

በአጠቃላይ ተደጋጋሚ ቤት የለሽ በሚለው አርእስት ብቁ ለመሆን ቤት የለሽ ለመሆንዎ ወይም ቤት የለሽ ለመሆን ችግር ከደረሰብዎ የሚገልጽ ታሪክ እንዲኖርዎት ያስፈልጋል። እንዲሁም ቤት እስኪያገኙ ድረስ በማቆያ አስተዳደር ወይም ኪሳራ ለደረሰበት መጠለያ ወኪል ሥር ባለው መጠለያ መኖር አለብዎት። የርስዎ ሁኔታ እንደዚህ ከሆነ ለቤቶች ጽ/ቤት ለማመልከት የማቆያ/ሽግግር ቤት ሥራ አስኪያጅ ይረዳዎታል።

## እርዳታ የሚሰጥበት መጠለያ (Support Housing)

በአጠቃላይ በእርዳታ የሚሰጥበት መጠለያ ለመመደብ ጠቃሚ የሆነ የግል እርዳታ ካስፈለገ፣ ለብቻ ለመኖር ለአካለ ስንኩላን ተብሎ በተዘጋጀ መጠለያ ወይም ለተሽከርካሪ ወንበር/ዊልቸር አመቺ የሆነ ቤት መሆን አለበት። አሁን የሚኖሩበት መጠለያ አመቺ ካልሆነ ምክንያቱም፡

- በሚኖሩበት ቤት ውስጥ ብዙ ለውጥ ካስፈለገው
- ለተሽከርካሪ ወንበር/ዊልቸር አመቺ ሆኖ ያልተሠራ ቤት
- ለሚደረገው ከባድ የህክምና ሁኔታ የሚያባብስ ከሆነ
- ለከባድ ሕመም ህክምና ከሚያደርጉበት ቦታ በጣም የራቀ ከሆነ

በተፈለገው አካባቢ ወይም የመኖሪያ ቤት ዓይነት ለማግኘት የቤቶች ጽ/ቤት ማስረጃ ይጠይቃል [ለምሳሌ ከሐኪምዎ ደብዳቤ]። ስለሚያስፈልጉ ነገሮች ዝርዝር ሁኔታ የቤቶች ጽ/ቤት ወይም የአቅራቢያዎ የኅብረተሰብ ድርጅት ሊሰጥዎት ይችላሉ [ማን ሊረዳኝ ይችላል? የሚለውን መመልከት]።

## ለየት ያለ የመኖሪያ ቤት ለሚፈልጉ (Special Housing Needs)

በአጠቃላይ እርስዎ ለየት ያለ የመኖሪያ ቤት ለሚፈልጉ በሚለው መደብ ለማመልከት የሚችሉት፡

- አሁን የሚኖሩበት መጠለያ ጊዚያዊ ከሆነና እንዲለቁ ተጠይቀው ከሆነ
- ድብደባ ወይም በቤተሰብ ውስጥ ችግር ይደርሳል ብለው የሚሰጉ ከሆነ ወይም
- የሚኖሩበት መጠለያ
  - በደባልነት የሚኖሩ ከሆነ ወይም በካራቫን ፓርክ ከሆነና ለርስዎና ለቤተሰብዎ የራሳችሁ የሆነ ማብሰያና የገላ መታጠቢያ ለማግኘት የማትችሉ ከሆነ
  - መጠኑ ወይም አካባቢው ከልጆችዎ ጋር ለመኖር ችግር የሚፈጥር ከሆነ
  - በጣም የተጣበበ ከሆነና ቢያንስ ሁለት የመኝታ ክፍሎች የሚያስፈልግ ከሆነ

- ለተለያዩ ፆታዎች የመኝታ ክፍሎቹ አመች ካልሆኑና ቢያንስ አንዱ ሰው ከስድስት ዓመት ዕድሜ በላይ ከሆነ ወይም ልጆች ከወላጆቻቸው ጋር በአንድ ክፍል ከሆኑ

- የሚኖሩበት መጠለያ ለጤነትዎ አመች ካልሆነ ወይም በቋሚነት እርስዎን ለሚንከባከብ ሠራተኛ በቂ ቦታ ከሌለውና የሚያሰጋ የሕክምና ሁኔታ ካለዎት ማመልከት ይችላሉ።

ለርስዎ ፍላጎትና ሁኔታ የትኛው መደብ እንደሚያስፈልግዎት እርግጠኛ ካልሆኑ የቤቶች ጽ/ቤትን ወይም በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የኀብረተሰብ ድርጅት ምክር መጠየቅ ነው [ማን ሊረዳኝ ይችላል? የሚለውን መመልከት]።

## ማመልከቻየን ከማስገባቴ በፊት ምን ማድረግ አለብኝ?

ማመልከቻዎን ወደ ቤቶች ጽ/ቤት ከማስገባትዎ በፊት ማድረግ ያለብዎት

- በማመልከቻው ቅጽ ውስጥ የሚገኙትን ክፍሎች ሁሉ ካሟሉ በኋላ ማንኛውንም ሰነድ አብሮ ማያያዝ [ለምሳሌ፡ የርስዎን ቪዛ ኮፒ፣ ከሴንተር ሊንክ የገቢ ሁኔታ የሚገልጽ ወረቀት፣ ከዶ/ርዎ የሕክምና ምርመራ የተደረገበትና በአስቸኳይ የመኖሪያ ቤት ለማስፈለጉ የሚገልጹ ሌሎች ሰነዶች]።

- የማመልከቻ ቅጹን በትክክል መሙላትዎንና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ሁሉ ማያያዝዎን ለማረጋገጥ የኀብረተሰብ ድርጅት ሠራተኛን ይጠይቁ።

- ምናልባት ማመልከቻዎ ከጠፋ ወይም ተቀባይነት ካላገኘ የሞሉትን ማመልከቻ ቅጽና የተያያዙትን ሰነዶች ፎቶ ኮፒ በማድረግ ማስረጃ እንዲሆን ነው።

## ማመልከቻየን ካስገባሁ በኋላ ምን ይደረጋል?

ማመልከቻዎን ካስገቡ በኋላ የቤቶች ጽ/ቤት ማመልከቻው መድረሱን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ይጽፍልዎታል [በ14 ቀናት ውስጥ]። ማመልከቻው መድረሱ ካልተገለጸልዎ የቤቶች ጽ/ቤትን ያናግሩ።

ብዙዎቹ የመንግሥት መኖሪያ ቤት ማመልከቻዎች በአጭር ሳምንታት ውስጥ ተከታትሎ መልስ ይሰጣል። የቤቶች ጽ/ቤት ያሳለፉትን ውሳኔ በጽሁፍ ለርስዎ መግለጽ አለባቸው። ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካገኘ የቤቶች ጽ/ቤት በመጠባበቂያ መዝገብ ወይም ለማመልከቻዎ መደብ ዓይነት በሚመጣጠን ዝርዝር ውስጥ ይመዘግብዎታል። ማመልከቻዎ ከጸደቀ በኋላ አድራሻዎን ከቀየሩ ለቤቶች ጽ/ቤት መናገር አይዘንጉ።

## ማመልከቻየ ተቀባይነት ካጣስ ምን ይደረጋል?

የቤቶች ጽ/ቤት በውሳኔ ስሕተት ፈጽመው ከሆነ ወይም ፖሊሲያቸውን በትክክል ካልተጠቀሙ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ። በቤቶች ጽ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ወይም ግልፅ የሆነ ቅሬታዎን ለበላይ አካል ይግባኝ ለማለት የተከራይ ማሕበርና ሌሎች የኀብረተሰብ ድርጅቶች ሊረድዎት ይችላሉ።

እንዲሁም ከጭቆና/ዲስክሪምኔሽን ለመከላከል መብት ይኖርዎታል። የርስዎን የጋብቻ ሁኔታ፣ ዘር፣ ፆታ፣ አካለ ስንኩል፣ በሽተኛ መሆን፣ የግብረ ስጋ ፍላጎት፣ ሃይማኖት ወይም ፖለቲካ መነሻ በማድረግ ለሚቀርቡ ማመልከቻዎች የቤቶች ጽ/ቤት አልቀበልም ማለት አይችልም። በነዚህ ላይ ልዩነት/ዲስክሪምኔሽን ተፈጥሮብኛል ብለው የሚያምኑ ከሆነ ካሣ ለማግኘት እንዲችሉ እንዲረዳዎት ለእኩል መብት ጠባቂ ኮሚሽን/ኢዐል ኦፖርቹኒቲ ኮሚሽን ማመልከት ነው። ለኢኳል ኦፖርቹኒቲ ኮሚሽን እንዲያመለክቱ የተከራዮች ማሕበርና ሌሎች የኀብረተሰብ ማሕበራት ሊረድዎት ይችላሉ።

## የመንግሥት ቤት እስኪሰጠን ለምን ያህል ጊዜ ያስጠብቀኛል?

የሚያስጠብቀው ጊዜ እንደ መኖሪያ ቤቱ ዓይነትና ያመለከቱበት አካባቢ ይወሰናል። ለምሳሌ፤ በከተማ ውስጥ በፎቅ ሕንፃ የምድር ቤት ለማግኘት የሚያስጠብቀው ጊዜ ተመሳሳይ መጠለያ ቤት ከከተማ ውጭ ለማግኘት ብዙ ጊዜ ያስጠብቃል። እንዲሁም ከአራትና ከዚያ በላይ መኝታ ክፍሎች ያለው መኖሪያ ቤት ለማግኘት እጥረት ስላለ ብዙ ጊዜ ያስጠብቃል።

የቆይታ ጊዜው ከሶስት ወራት እስከ ብዙ ዓመታት ሊፈጅ ሲችል የርስዎ ሁኔታ ይወስነዋል። በአጠቃላይ በተደጋጋሚ ቤት አጥ በሚለው መደብ ውስጥ ለሆኑ ሰዎች በቅድሚያ የመጠለያ ቤት ይሰጣል። በእርዳታ የሚሰጥበት መጠለያ መደብ በሚለው ላመለከቱ ሰዎች በሁለተኛ ደረጃ ሲሰጥ ቀጥሎም ለየት ያለ የመኖሪያ ቤት ለሚፈልጉ በሚለው መደብ ላመለከቱ ይሰጣል። ተራ-መጠበቅ በሚለው መደብ ላይ ካመለከቱ የሚያስጠብቀው ጊዜ ለብዙ ዓመታት ሊሆን ይችላል።

## ስንት ምርጫዎች ናቸው የሚሰጡኝ?

በተደጋጋሚ ቤት አጥ፣ እርዳታ በሚሰጥበት መጠለያ ወይም ለየት ያለ የመኖሪያ ቤት ለሚፈልጉ በሚለው መደብ የቤቶች ጽ/ቤት ማመልከቻዎን ከመደበው አንድ የመኖሪያ ቤት ይቀርብልዎታል። ይህንን አልቀበልም ካሉ በቀጥታ ተራ-መጠበቅ በሚለው መደብ ላይ ይመዘገባሉ። የቀረበልዎት መጠለያ ቤት በአንዳንድ ሁኔታ የርስዎን የሕክምና ወይም የተለየ ፍላጎት የማያሟላ ከሆነ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ።

በተጨማሪ ከተራ-መጠበቅ በሚለው መዝገብ የቀረበልዎትን መጠለያ ቤት አልቀበልም ካሉ ከሁሉም ምዝገባ ላይ ስምዎ ይሰረዛል። ስምዎ መጀመሪያ ተራ-መጠበቅ በሚለው መደብ ላይ ተመዝግቦ ከሆነ ሁለት የመንግሥት መኖሪያ ቤት ምርጫዎች ይቀርብልዎታል።

ቤቱ የተዘጋጀ ለመሆኑ ለማሳወቅ የቤቶች ጽ/ቤት በደብዳቤ ያሳውቅዎታል። በተቻለ ፍጥነት ስለቀረበልዎት ቤት መልስ እንዲሰጡ ይጠየቃሉ። እንዲሁም ማመልከቻውን ካስገቡበት ጊዜ ጀምሮ በርስዎ ላይ የሆነ ለውጥ ካለ የቤቶች ጽ/ቤት ይጠይቅዎታል።

## የመንግሥት ቤት ተከራይ ከሆኑኩ በኋላ የሚኖረኝ መብትና ግዴታዎች ምን'ድን ናቸው?

በቤቶች ጽ/ቤት በኩል ቤት ከተሰጥዎ በኋላ የተከራይና አካራይ ስምምነት ወይም ውል እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ። ይህ ህጋዊ ስምምነት ሲሆን በርስዎና በቤቶች ጽ/ቤት መካከል ይደረጋል። ይህ ሰነድ ካልተረዳዎት ወይም ጥያቄ ካለዎት በአቅራቢያዎ ያለውን የኅብረተሰብ ድርጅት ያናግሩ [ማን ሊረዳኝ ይችላል? የሚለውን መመልከት]።

አንዴ ውሉን ከፈረሙ በኋላ እንደ ሌሎች የቪክቶሪያ ተከራዮች መብትና ግዴታዎች ይኖርዎታል። [ መብትና ግዴታን የሚገልጽ ጽሑፍ በተከራዮች ማሕበር በነፃ ሊሰጥዎት ይችላል]።

## ማን ሊረዳኝ ይችላል?

የሚከተሉት አገልግሎቶች በነፃ፣ ምስጢራዊና ለብቻ ከቤቶች ጽ/ቤት ውጭ ሆኖ ይቀርባል። ስለ መንግሥት መኖሪያ ቤቶች ማመልከቻና ስላልተያዙ ቤቶች በማሳወቅ ዕውቀት ስላላቸው የርስዎን ማመልከቻ በመሙላት ሊረዱ ይችላሉ።

## የመንግሥት ቤት ተከራይ የምክር አገልግሎት (Public Tenant Services)

በሚኖርዎት ሕጋዊ መብቶች እንደ የመንግሥት መኖሪያ ቤት አመልካች የመንግሥት ቤት ተከራይ የምክር አገልግሎት ሊያቀርብልዎት ይችላል። እነዚህም፧

- ለመንግሥት መኖሪያ ቤት የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት መርዳት
- ለመንግሥት መኖሪያ ቤት የገቢና የንብረት መጠን ወቅታዊ ዝርዝር ማቅረብ
- የቤቶች ጽ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ አቤቱታ ለማቅረብ መርዳት
- ከቤቶች ጽ/ቤት ጋር ችግር ካለዎት መርዳት
- ስለ መንግሥት መኖሪያ ቤት ጉዳይ የርስዎን ኅብረተሰብ ቡድን ማናገር
- እርስዎን ወደ ሌላ ማሕበረሰብ ድርጅቶች መላክ

ከነዚህ አገልግሎቶች ውስጥ የተከራይ ማሕበር አንዱ ነው። የተከራይ ማሕበር ለማናገር በስልክ 9416 2577 ወይም በ12 ቋንቋዎች መረጃ ለማግኘት የተከራይ ማሕበር ዌብ ሳይት (www.tuv.org.au) መጎብኘት እንዲሁም ለዝርዝሩ በቪክቶሪያ ዙሪያ ያሉትን የሕብረተሰብ ድርጅቶች ማናገር ነው። አስተርጓሚ ካስፈለግዎት በስልክ አስተርጓሚ አገልግሎት 131 450 በመደወል የተከራይ ማሕበርን ማናገር።

## የመሸጋገሪያ መኖሪያ ቤት አስተዳደሮች

የመሸጋገሪያ መኖሪያ ቤት አስተዳደሮች ለተወሰነ ጊዜ ገደብ መጠለያ ከዚህ ለሚከተለው ያቀርባል፡

- ቤት ለሌለው ወይም የቤት ችግር ላጋጠመው ቤተሰብና ብቻውን ለሚኖር ሰው
- ከቤተሰብ ጠብ/ግጭት ገለል ላሉ ሴቶችና ህፃናት
- ቤት ለሌላቸውና ከቤተሰብ ጠብ/ግጭት ላመለጡ ወጣቶች [ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 25] ለሆኑ

በመሸጋገሪያ መኖሪያ ከገቡ በኋላ ቤት ላጣ በሚለው የመንግሥት መኖሪያ ቤት ለማመልከት የርስዎ የመሸጋገሪያ መኖሪያ ቤት አስተዳዳሪ ሊረዳዎት ይችላል።

## የመጤ/ስደተኛ ምንጭ ማእከላት (Migrant Resource Centres)

በኅብረተሰብዎ ውስጥ ስላለው የመረጃ አገልግሎት በቋንቋዎ የመጤ/ስደተኛ ምንጭ ማእከላት ሊሰጡ ይችላሉ። በነዚህ ማእከላት ውስጥ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ሌላ የሚናገሩ ሠራተኞች አሏቸው። በአቀራቢያዎ ያለውን የመጤ/ስደተኛ ምንጭ ማእከላት ለማግኘት ድርጅት/ማይግራንት በሚለው የስልክ ማውጫ የለው ፔጆስ L-Z ይመልከቱ።